# አዳም ረታ እንደ postcolonial ፈላስፋ

*Teshale Kebede Bedriya*

"…ቅኝ አልተገዛንም ብለው ጉራ እየነፉ በየቀኑ ግን የተገዥነት አገልግሎት ይሰጣሉ" (የስንብት ቀለማት፣24)

አዳም ረታ በተለይ ኋላ ላይ ባሳተማቸው 'እቴሜቴ የሎሚ ሽታ' እና 'የስንብት ቀለማት' ውስጥ የ-postcolonialism ፍልስፍናዊ እሳቤዎችን ጎልቶ ይንጸባረቅባቸዋል፡፡

አድዋ ላይ ቅኝ ገዥዎችን ድል አድርገን መልሰናል የሚለው ኩራታችን አፋዊ እንጂ ከልብ የመነጨ እንዳልሆነ በላቀ ኪናዊ ውበትና ጥልቅ መረዳቱን ገልጦ አስነብቦናል፡፡ ነጻነታችንን እና የስልጣኔ አሻራዎቻችን እንደልቃቂት አውጥተን ጥለን ፈረንጅ ለመምሰል የተጋጋጥንባቸው የሕማም ዓመታት እንደገና እንድናጤናቸው በድርሰቶቹ ብዙ ገስጾናል፡፡ እኛ ግን ከራሳችን ጋር መታረቅ ተስኖን እዚያው'ጋ ነን… እንደመነሻ፣ ከድህረ-አድዋ በኋላ እንደወረደ ተቀብለን ከተጋትናቸው ጉዳዮች መካከል እውቅት፣ ስልጣኔ፣ የተቋማት ግንባታ፣ ቁሳዊ ልማት፣ ርዕዮታዊ መረዳት…ከውጭ ሃገር እንደሸቀጥ አምጥቶ በየቦታው የሚከፋፈል አድርጎ የመረዳት ሥሁት ግንዛቤ አንዱ ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ እውቀት በተውሶ ለማምጣት ከአንዱ ሃገር ወደ ሌላ ሀገር ስንዞር አንድ አንድ ክፍለዘመን ተሻገርን፡፡ በሃገር ውስጥ በፈረንጅ አፍ እያወራን በስልጣኔ ብርሃን ለመጥለቅለቅ በሚል የቋንቋ ትምህርት ቤቶች ከፈትን፡፡ "የአውሮፓ የስልጣኔ መንገድ" በመከተል ካለንበት 'ጨለማ ወጥተን' ልክ እንደ'ሰለጠኑት' ሃገራት በ'ብርሃን' መንገድ ለመጓዝ በሚል እዚህም እዚያም ባጀን፡፡

ኋላ ላይ የመጡት መንግስታትና የፖለቲካ ልሂቃንም አንዴ ሶሻሊዝም ሌላ ጊዜ የልማታዊ መንግስት ሞዴል አምጥተው ለመተግበር ሞከሩ፡፡ ሙከራው ግን ከቀውስ ወደ ቀውስ ከመሸጋገር ያለፈ አንድ ስንዝር እንኳ ፈቅ እንድንል አላገዘንም፡፡ለምን?...

አዳም ይህንን የህማም ጉዟችንን እንደ ከያኒ ሥነውበታዊ ፍኖቱን ሳይለቅ፤ እንደ አሳቢ ደግሞ ከሥነዕውቀታዊ ከፍታው ሳይወርድ ገልጦ ያሳየናል፡፡ ታመን እንዳልታመምን በማስመሰል የመጣንበትን ሥሁት መንገድ ዳግም እንድናጤነው ይወተውተናል፡፡ ከህማማችን የምንፈወስበት መውጫ መንገዱን ጭምር ይጠቁመናል፡፡

እዚህ'ጋ ለማስታወስ ያህል postcolonialism የቁም ፍቺው እንደሚያመለክተው ከ-colonialism ቀጥሎ የሚመጣ ሥርዓት ሳይሆን፣ የኮሎኒያሊዝም ሌጋሲዎችን በተዘዋዋሪ መንገድ በድህረ ቅኝ ግዛት የቀጠሉ መሆኑንና ይህም በሃገሬው ነባር ባህል፣ ዕውቀት፣ እሴት፣ ማህበራዊ መስተጋብር…ላይ ከፍተኛ ተቃርኖ እንደፈጠረ የሚያትት ዕሳቤ ነው፡፡

አፍሪካዊው ፈላስፋ Valentin Mudimbe 'The Invention of Africa' በተሰኘው መጽሃፉ እንዳሰፈረው፣Colonialism ማለት ቅኝገዥዎች የቅኝ ተገዥውን ሃገርና ማህበረሰብ በሃይል በመቆጣጠር አንድም የተፈጥሮ ሃብቱን አሟጦ ወደ ምዕራቡ ዓለም የመላክ ሲሆን፣ ይህንን ብዝበዛ ቀጣይነት እንዲኖረው ደግሞ የቅኝተገዥው ማህበረሰብ ማንነታዊ መሰረት እንደገና የማዋቀርና የመቅረጽ ስራ ይሰራል፡፡ በሌላ በኩል ማንነትን እንደገና የመበየንና የመቅረጽ ሂደት የስልጣን ተዋረዱ ሳይዛነፍ

እንዲቀጥል፣ ቅኝ ተገዥዎች በዚህ የሃይል ተዋረድ ቦታቸው የተገዥነትና ጥገኝነት መሆኑን በሥነዕውቀታዊ፣ በተረክና በሌሎችም ይስሙላ ሳይንሳዊ ምርምሮቻቸው ላይ እውነታነት እንዳለው የሚያትት ዕሳቤ ነው፡፡

ህንዳዊቷ ፕ/ር Ania Loomba ታዲያ 'Colonialism/ Postcolonialism' በተሰኘው መጽሃፏ ይህንን የቅኝ ግዛታዊ ዲስኮርስና ተረክ ከስር መሰረቱ መረዳትና ይኸ ተረክ በድህረ-ቅኝግዛት ዘመንም እንዴት እንደቀጠለ ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው ትላለች፡፡ ቅኝአገዛዝ በታሪክ ሁለትዮሻዊ ተቃርኖ (binary opposition) በመፍጠር አደገኛና ውስብስብ ተረኮችን ፈጥሯል፡፡ አውሮፓን ወይም ምእራቡ ዓለም "እኛ" በሚለው ጎራ ውስጥ በማስገባት "ከምዕራቡ ዓለም ውጪ ያለውን ማህበረሰብ ደግሞ "ሌሎች" (others) በሚለው ጎራ መድቧቸዋል፡፡ ይህን የሁለትዮሻዊ ዓለም (west-east) ተረክ አውሮፓውያን ለራሳቸው ያላቸውን ምስልና ከአውሮፓ ውጭ ባሉ ሕዝቦች መካከል አለ የሚሉትን የልዩነት መስመር ለማስመር ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡

ለአብነትም አውሮፓውያን "የሰለጠኑ"፣ በ"አመክንዮ ታግዘው ማሰብ የሚችሉ"ና ዕውቀታቸው ለሌሎችም "አርዓያ መሆን የሚችል" አድርገው ሲቀርጹት፤ በአንጻሩ ከአውሮፓ ውጪ ያለው ማህበረሰብ ደግሞ "ያልሰለጠነ"፣ ስሜቱን "መግራት ያልቻለ" አድርገው ፈርጀውታል፡፡ እንዲሁም ነባር ባህሉንና እሴቱን እድገትና ለውጥ ለማምጣት የ"ማያስችል" አድርገው በይስሙላ ሳይንሳዊ ጥናቶቻቸው ጭምር አስደግፈው ለማሳመን ችሏል፡፡

ታዲያ ከ19ኛው ክ/ዘ አንስቶ እየኖርንባት ያለችው ይህች ዓለም በዚህ ቅኝት ነው የተበጃጀችው፡፡ ቅኝአገዛዝ "አበቃ" ቢባልም መልኩን በመቀየር ከአውሮፓ ውጭ ባሉ ሃገራት የትምህርት ስርዓት፣ የመንግስት አወቃቀር፣ የባህል ዘርፍ…ውስጥ ሰርጾ በመግባት ህልውናውን ማስቀጠል ችሏል፡፡ የ-postcolonial አሳብያንና ስራዎቻቸውም ከትናንት የተሻገሩ የቅኝገዥዎች ሌጋሲዎቻቸውን በዛሬው አስተሳሰባችን፣ የህይወት ዘይቤያችንና ተቋሞቻችን ውስጥ እንዴት ተተግባሪ እንደሚሆኑ ያሳዩናል፡፡

አዳም ልክ እንደ postcolonial ፈላስፎች፣ ቅኝ ገዥዎች ሃገራችንን በሃይል ወርረው በመያዝ ለዓመታት ባይቆዩም፣ ቅኝግዛታዊ አስተሳሰባቸውን፣ የህይወት ዘይቤያቸውን፣ የአገዛዝ ስልታቸውንና ዕቅዳቸውን አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ተቀብለን እየተገበርነውና እየኖርነው እንዳለ ከመጣንበት የትናንትናው መንገድ ሰበዞችን እየመዘዘ ይወቅሰናል፡፡

"ባዴ [ፈረንጅ] የተለየ ብሩህ አይደለም ብለው የነዘነዙኝ በባዴ ቅኝ ገዥዎች ራሳቸውን እንዲጠሉ ጥልቅ ትምህርት የወሰዱና ዛሬም ከእነሱ እግር ስር የማይጠፉ ወገናቸውን ባዴ በቀደደላቸው መንገድ የሚቀረቅቡ ነጋዴዎች ናቸው፡፡" (ስ.ቀ፣ 23)-ይህን የተባሉት ራሱን የ"ወርቃማው ትውልድ" ወይም የ"ያ ትውልድ" አባላት ነው ለሚሉት አብዮተኞች የተሰነዘረች ትችት ነች፡፡

ትልቁ አሳቢና ሳይካትሪስት ፍራንዝ ፋኖን 'Black Skin White Mask' በተሰኘው መጽሃፉ የጥቁሮች የበታችነት ሥሜት (Inferiority complex) ምንጩ የ" Colonial discourse" ነው ይላል፤ "…colonialism not only exploits but dehumanize and objectifies the colonized subject." ፋኖን የቅኝ ግዛታዊ ዲስኮርስ በቅኝ ገዢው ግለሰብ ሥነ-ልቦና ውስጥ እንዲሰርጽ ያደረገበት መንገድ ደግሞ ግለሰቡ የወጣበትን ማህበረሰብ ታሪኩን፣ ማህበራዊ እሴቱን ዋጋ በማሳጣትና በማጥፋት በማጥፋት ከትውስታው ማህደር እንዲፋቅ በማድረግ በምትኩ የነጭ የበላይነት ተፈጥሮአዊ አድርጎ የሚቀበልና እሱን ለመምሰል የሚሞክር ግለሰብ ሆኗል ይለናል፡፡

"…የአገራችንን መልካም ታሪክ እንጥቀስ ስንል ዐይኖቻቸው ቀልተው 'the past is a foreign country' (ያለፈው ዘመን ባዕድ አገር ነው) ይሉናል፡፡…የነጭና የጥቁር ተራቾች ግን ታሪክ አስፈላጊ አይደለም……ያውም ደብተራ የዘባረቀው ብለው ለምን የታሪክ ምሁር እንደሆኑ ግን አይነግሩንም፡፡ …የባዕድ ደብተራ የጻፈውን ግን ያምኑታል፡፡"(ስ.ቀ፣ 23)

ያለፈውን ታሪክ፣ የማህበረሰቡን ዕሴትና ዕውቀት በጭፍን ማጥላላትና መናቅ የመሰልጠን መንገድ አድርገን እየሄድንበት ያለው መንገድ ቆም ብለን ለመረዳት እንኳ ጊዜ ያለን አይመስልም፡፡ የማጥላላት ዘመቻውም የሚያጋፍረው መድረኩን የያዘው ዘመንኩ ወይም ተማርኩ ባዩ ነው፡፡

ፈላስፋው Valentin Mudimbe ከላይ በጠቀስኩት መጽሃፉ እንዳሰፈረው፣ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ቢያንስ ነጭ ቅኝገዥዎች የአፍሪካን መሬት ለቀው ቢወጡም በእነሱ ቦታ "ጥቁር ቅኝገዥዎች" ወይም ልሂቃን ተተክቷል፡፡ በምዕራቡ ዓለም የቅኝግዛታዊ ዲስኮርስና ዕውቀት ተኮትኩተው ያደጉት አፍሪካውያን ቀድሞ ቅኝ ገዢዎች ሲከውኑት የነበረውን ነገር በአንድም ሆነ በሌላ አቅጣጫ ቀጠለ እንጂ አልተቋረጠም፡፡ ነጭ ቅኝ ገዥዎች የተኩት አፍሪካውያን የፖለቲካ ልሂቃን ከምዕራቡ ዓለም ሥርዓት ወይም ተቋማት ጋር ያላቸው ግንኙነት የጌታና የሎሌ ወይም የጥገኝነት እንዲሆን ያደረገውም ይኸው የቅኝአገዛዝ ሌጋሲ ነው፤" …colonialism should have produced a body of knowledge on the means of exploting dependencies."

በሃገራችን ኢትዮጵያም የሆነውና እየሆነ ያለው ይኸው የቅኝ አገዛዝ ማዕከላዊ እሳቤ ከትምህርት ስርዓታችን አንስቶ እስከ ፖለቲካዊ መድረኮች ተሞልቷል፡፡ እውቀት ከሌሎች ሃገራት ተፈልጎ የሚመጣ እንጂ ከራሳችን አንጥረን ማውጣት እንደምንችል ሊገለጥልን እንዳልቻለ የምዕተ-ዓመት ጉዟችን ምስክር ነው፡፡ አዳምም ይህንን በደመነፍስ የሚደረግ ጉዞ አጥብቆ ይተቻል፡፡

"የኢትዮጵያ ምሁራን ሲሰለጥኑና ዘሮቻቸውን ሊያሰለጥኑ ሲፈልጉ መጽሃፎች ይጽፋሉ፡፡ በነዚህ መጽሃፎች ውስጥ የሚጠይቁት አንድ ዋነኛ ጥያቄ እኔ ምን አለኝ? ሳይሆን እነሱ ምን አላቸው? ነው አሉ፡፡ …ካላመናችሁ ጃፓን እንደምን ሰለጠነችን አንብቡ፡፡" (785)

ፕ/ር ማዕምር መናሰማይ "A Critical Dialogue between Fifteen and Twenty first Century Ethiopia"በተሰኘው ጥናታቸው ያለፉትን ሶስት የመንግስት ስርዓቶችን (አጼ ኃይለ ሥላሴ፣ ደርግና ኢህአዴግ)ኢትዮጵያን ለማዘመን የሄዱበት መንገድና ዘይቤ "ፍዝዝመና" (passive modernization) ሲሉ ሰይመውታል፡፡ ይህም ማለት በልማት ስም ምዕራባዊ ለመምሰል መሞከር፣ በምዕራቡ ዕውቀትና ሥነ-ዘዴ ላይ በመመስረት ልማት ለማምጣት ያደረጉትን ያልተሳካ ሙከራ ነው ፍዝ ዝመና ብለው የጠሩት።፡

ይህ ፍዝ ዝመና ሃገር በቀል ዕውቀቶችን፣ እሴቶችን፣ እይታዎችንና ባህሎችንና ተቋማትን አፈራርሶ በምዕራቡ እሳቤ የመተካት ሙከራ ነው ይላሉ። የዚህ ውጤትም በሃገሪቱ ውስጥ መልከ-ብዙ ቀውስና ምስቅልቅሎሾችን አስከትሏል፡፡ "…the failure of modernization in Ethiopia is also the failure of knowledge: of Ethiopia and of modernization."

አዳም ረታ በ'እቴሜቴ ሎሚ ሽታ' በሰዓሊና በሃያሲ መስኮት ገረሱ በኩል የዘመኑን ሁኔታ እንዲተነትን፣ እንዲተችና እንዲተረጉም አጭቶታል፡፡ መስኮት በተለይ ፈረንጅ ያልነካው ወይም 'ያልባረከው' ነገር ፋይዳ ቢስ ለሚያደርጉና የፈረንጅ እውቀት የሁሉም ነገር መመዘኛ አድርገው ለተቀበሉ የዘመኑ ወጣቶችን

በየጋዜጣው ይተቻል፡፡ ሃገር በቀል እሴቶቻችንም ወደ መድረኩ ይመልሳቸዋል፣ ይተነትናቸዋል፣ አንዳች እውነት ፈልቅቆ ለማውጣት ይተጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ መስኮት አስቀድሞ ይከተለው የነበረው የ"አብስትራክት ኤክስፐረሺንንዝም" የአሳሳል ዘይቤ በመተው፣ የሃገር በቀል ዕውቀትና experience መሰረት ያደረገ "ተነካናኪ" ወይም "ቅርባዊነት" የተሰኘ የአሳሳል ዘይቤ ፈጥሯል፡፡ ክፍለ ዘመን የተሸገረው የተቃወሰው ጉዟችን ዳግም መታደስ የሚችለው፤ ከራሳችን ጋር እርቅ አውርደን ነጋችንን ለማሳመር የመስኮት ገረሱን ፈለግ ከመከተል የተሻለ ሌላ ምን ምርጫ ሊኖረን ይችላል?!